Seattle Public Schools

# የ2023-24 የቤተሰቦች የይግባኝ መመሪያ

ለተማሪዎቾ አካዴሚያዊ ስኬት ስላሳዩት እምነት እና አጋርነት እናመሰግናለን።የላቀ ትምህርት ዲፓርትመነት ከየላቀ ትምህርት ይግባኝ ሂደት በፊት፣ወቅት እና በኋላ መመሪያ ለመስጠት ይጥራል (WAC 392-170-076)።ቤተሰቦች ተማሪያቸው ለላቀ ትምህርት አገልግሎት ብቁ ሆኖ ካልተገኘ ይግባኝ ማለት ይችላሉ።በሁለንተናዊ ማጣርያ ጊዜ የቀረቡትን ልዩ ሁኔታዎች(exceptional circumstances) ወይም የጎደሉ የ objective/subjective መመዘኛዎች ማረጋገጫ ሊኖራቸው ይገባል።

ይአንድ ይግባኝ ከሰነዶች/ማስረጃዎች ጋር (ለይግባኝዎ አስፈላጊ ከሆነ) ከገባ በኋላ፣የላቀ ትምህርት ዲፓርትመንት በ የይግባኙ ግምገማው ወቅት ከግምት ውስጥ የሚገቡ ተጨማሪ መረጃዎች ወይም ሰነዶች አይቀበልም።

**የይግባኝ ቅፆች የመጨረሻ የማስገብያ ቀን ማክሰኞ፣የካቲት 20 ነው**

## ለመጀመር

ይግባኝ ከማቅረብዎ በፊት፣እባክዎ የሚከተሉትን ሰነዶች ለማግኘት ትንሽ ጊዜ ይውሰዱ።

- ☐ የተማሪ ብቁነት ደብዳቤ።
  - ይህ ደብዳቤ/ውጤት በየሶርስ መለያዎ(Source account) ይገኛል።
- ☐ ስላሉት የይግባኝ አይነቶች መረጃ እና የጊዜ ገደብ።
  - ይህ በላቀ ትምህርት ድረ-ገጽ(Advanced Learning web page) ላይ ይገኛል።
- ☐ የይግባኝ ቅፅ በላቀ ትምህርት ድረ-ገጽ( Advanced Learning web page )እና በተማሪዎ የብቃት ደብዳቤ ላይ ይገኛል።
  - እነዚህ በአማርኛ፣በቀላል ቻይንኛ፣በእንግሊዝኛ፣በሶማሊኛ፣በስፓኒሽ እና በቬትናምኛ ይገኛል።.
- ☐ የልዩ ሁኔታ(special circumstance) ወይም የጎደሉትን የ objective እና/ወይም የ subjective መመዘኛዎች እና የትምህርት ሰራተኞች ደጋፊ ሰነዶች ማብራሪያ ማዘጋጀት።
  - ይህ መረጃ ወደ advlearn2@seattleschools.orgመላክ አለበት።ለቀላል ሂደት እባኮትን በርዕሰ ጉዳዩ መስመር ላይ "ይግባኝ(" Appeal")" ብለው ይፃፉ።

የይግባኝ ቅጹን ለመሙላት የትርጉም አገልግሎቶች አስፈላጊ ከሆን ፣እባክዎን የላቀ ትምህርት የደንበኛ እንክብካቤ ቡድንን(Advanced Learning Customer Care Team) በ advlearn2@seattleschools.org ያነጋግሩ።

## ይግባኙን ማጠናቀቅ

ቤተሰቦች ለይግባኝ ከሁለቱ አማራጮች አንዱን መምረጥ አለባቸው፡- **Conditional** or **Identification**

ይግባኝዎ በእነዚህ ሁለት ምድቦች ውስጥ የማይካተት ከሆነ፣ይግባኝዎ አይገመገምም፣እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ከዚህ መረጃ ጋር የማሳወቂያ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል።አንዳንድ ቤተሰቦች በሂደቱ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ግምገማዎች ልጃቸው የላቀ ትምህርት አገልግሎት እንደሚያስፈልገው በትክክል አላሳዩም ወይም መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ ልጃቸው ከፍተኛ እድገት እንዳሳየ ሊሰማቸው ይችላል።ይህ ትክክለኛ ይግባኝ አይደለም።

### ሁኔታዊ ይግባኝ (Conditional Appeals)

አንድ ሁኔታ ወይም ሁኔታ(condition or circumstance) ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የማይገኝ መረጃን እንደፈጠረ ከታመነ።.

- ምሳሌ 1: ተማሪዬ በጠቅላላው የአካዳሚክ ግስጋሴ (MAP) ግምገማ ጊዜ ታሞ እንደነበረ ፣ እና ይህ በዶክተር ማስታወሻ እና በርእሰ መምህር ደብዳቤ ከተረጋገጠ።
- ምሳሌ 2: በግምገማው ወቅት የተማሪዬ አይፓድ በሌላ ተማሪ ከተወሰደ።ይህ ወዲያውኑ ለመምህሩ ሪፖርት ከተደረገ እና ከርዕሰ መምህሩ ጋር በመሆን ሁኔታውን ከተረጋገጠ።
- ምሳሌ 3: The Demonstrated Performance Tool (DPT) ወይም MAP ለልጄ ካልተዘጋጀ  እና  እናዳይሰጠው ብየ ካልመረጥኩ።

**ይግባኝ ሰሚው አካል መሰብሰብ እና በጽሁፍ መቅረብ ያለበት:**
*በሁኔታ ወይም ሁኔታ(condition or circumstance)ምክንያት የተማሪውን የብቃት መለያ ውጤት ትክክል አይደለም ብለው የሚያምኑበትን ምክንያት የሚገልጽ ማብራሪያ እና ማስረጃ እና ለምን የተለየ ነገር መደረግ እንዳለበት አሳማኝ ምክንያት።*

## የመለየት ይግባኝ (Identification Appeals)
*ለመለየት ጥቅም ላይ የዋለውን መረጃ ስህተት ነበረው።ይህ ተማሪው ለአገልግሎት ብቁ እንዳይሆን ካደረገው።*

- *ምሳሌ: መምህሩ እና ርእሰ መምህሩ የግምገማው መረጃ በስርአቱ ውስጥ በትክክል አለመጫኑን ካረጋገጡ። ይግባኝ ሰሚው አካል መሰብሰብ እና በጽሁፍ መቅረብ ያለበት::*

**ይግባኝ ሰሚው አካል መሰብሰብ እና በጽሁፍ መቅረብ ያለበት::**
ለመለየት ጥቅም ላይ በዋለው መረጃ ላይ ስህተት መኖሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የሚያሳይ ማብራሪያ።

## ቀጥሎ ምን ይሆናል?

ይግባኙ አንደ ከቀረበ በኋላ፣የብዙ ዲሲፕሊን ምርጫ (MSC) ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ይሰበሰባል፣እያንዳንዱን የይግባኝ ቅፅ እና የመጀመሪያውን የብቃት ውሳኔ ለማድረግ ጥቅም ላይ የዋለውን መረጃ ይገመግማል፣ከዚያ የይግባኙን ውሳኔ ይሰጣል።

የMSC ይግባኝ ኮሚቴ የሰለጠኑ አስተማሪዎች እና ሌሎች እንደ አማካሪዎች፣አስተማሪዎች እና የዲስትሪክት መሪዎች ያሉ ሙያዊ ሰራተኞችን ያቀፈ ነው።ኮሚቴው በይግባኝ ጊዜ የገባውን የተማሪ ዳታ/መረጃ ይገመግማል እንዲሁም ይግባኙ ትክክል መሆኑን ከወሰነ በብቃት ውሳኔው ላይ ለውጥ ያመጣል።

ኮሚቴው የይግባኝ ግምገማቸውን ካጠናቀቀ በኋላ፣የይግባኝ ቅጹን በደረሳቸው በ25 የትምህርት ቀናት ውስጥ ለቤተሰቦች የጽሁፍ ውሳኔ ይሰጣል።

የMSC ይግባኝ ኮሚቴ በዓመት ለአንድ ተማሪ **አንድ** ይግባኝ ይገመግማል።

በክልል ህግ መሰረት፣በዲስትሪክቱ ባለስልጣን የመጨረሻ ውሳኔ ያልተደሰተ ማንኛውም ሰው ውሳኔው ከተላለፈ በ30 ቀናት ውስጥ ወደ ኪንግ ካውንቲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማለት ይችላል.

ተጨማሪ ጥያቄዎች? በ advlearn2@seattleschools.org ያነጋግሩ።